# የተሰደዱ ጠጉሮች

*የጊዜ ዑደቱ በራስ ላይ የመጣ፣*
*ወለላዬም ሽበት ትንሣዔም መላጣ።*
*ሆነን አየንና በዘመን መስተዋት፣*
*ቁልቁልም ወረድን ወጣንም አቀበት፤*
*ግራ ኢጋባንና መመለጥ መሸበት።*
*ተረት ሆነን ልንሞት ታሪክ ሳንሰራ፣*
*ብልጭ ብለን ጥፍት እንደ ባለ ተራ።*
*እያልኩ ሳስተውል ሳስብ ስመረምር፣*
*እጅግ ጥልቅ ሆነብኝ የተፈጥሮ ምስጢር።*

*መመለጥም ይሁን የመሸበት ጣጣ፣*
*ምንጩ ከውስጥ ነው ፈንቅሎ እሚወጣ።*
*የንጥረ ነገር እጦት በማነሱ መብል፣*
*የከባቢው አየር ሂደቱን ሲያጋግል።*
*የራስ ቅል ኢጋላጭ ጠሰኛው መላጣ፣*
*ለካስ መገንጠሉ በዘር ነው እሚመጣ።*

*ብርዱንና ቁሩን ተጋፍጦ ፊት ለፊት፣*
*ሽፍኖ በኖረ ይህን የኔን አናት፤*
*በብሩሽም ስልግ ሳበጥር ጎፈሬ፣*
*እንዳሻህ ያለኝን ላንተ ነው መኖሬ፤*
*በጅ የያዙት ነገር ንቄው ከገለባ፣*
*እኔው አጣጣልኩት እንደ ጥቅም አልባ።*

*ከአናቴ ያልተለዩ በደጉም በክፉ፣*
*ጠጉሮችም ነበሩኝ ከራሴ የጠፉ።*
*ያልተንበረከኩ ቅጫም ሲንሰራፋ፣*
*ቆም ቆም የሚሉ ሰናደድ ስከፋ።*
*ቅባት ጠፋ ብለው ያልተንከረደዱ፣*
*ከራስ ቅል መለየት ጨርሶ እማይወዱ።*

*ለካስ አሉኝ ጠጉሮች ከኔ ያልተለዩ፣*
*በስደት ስፍራ ላይ መከራ የሚያዩ።*
*የሚበጠር ጠጉር ከአናቴ የጠፋ፣*
*እነርሱ በቅለው ነው በገደል በፈፋ።*

*አወይ ስደት ክፉ ሁሉን የሚያሳንስ፣*
*መጠየፍ አይችልም ቆሻሻ ግሳንግስ።*
*ከአናት ተኮፍሶ እንዳልኖረ ኮርቶ፣*
*በአፍንጫ ቀዳዳ ይውላል ተኝቶ።*
*ደምቆ እሚበቅልበት የራስ ቅል ሳይጠፋ፣*
*ንፍጥ ውስጥ እየዋኘ ይኖራል በተስፋ።*
*ካልጠፋበት ቦታ የራስ ቅሉ ሜዳ፣*
*ጎፈሬ በቀለ በአፍንጫ ቀዳዳ።*

*ሌቶች ኢያነሱ ቀኖች ኢያጠሩ፣*
*አወይ የእድሜ ነገር መሮጡ መብረሩ።*
*የተገፉት ጠጉሮች ከመሀል እራሴ የተነቃቀሉ፣*
*ሰደት መረጡና ቀን እስቲያልፍ እያሉ፤*
*ጆሮ ኩስ ላይ በቅለው ይተራመሳሉ።*

*ስደት መንከራተት መች አሸነፋቸው፣*
*የወዛቸው ማማር የአጠቋቆራቸው፤*
*ከቀጭኔ ጭራ ባይበልጥም እኩል ነው።*
*ይሁን ተመስገን ነው አለኝ ማለት ደጉ፣*
*ሰዋራ ስፍራም ቢሆን ይኑሩ ይደጉ።*
*የብብት፣ ያፍንጫ የጆሮም ቢባሉ፣*
*ይብዙ እንጂ ይባዙ ይኑሩ ይብቀሉ፣*
*በጥቅል ሲጠሩ ጠጉርም አይደሉ?*
*ፊደል እየገደፉ አሉ እንጂ መላ አጣ፣*
*የኔስ መጠርያዬ መላ አምጣ መላ አምጣ።*

ከርስታቸው ከራስ ቅል መገንጠል ግድ ለሆነባቸው እንዲሁም ስደት ቁልቁል ላወረዳቸው ጠጉሮች መታሰብያ ይሁን። ነጥተውም ገርጥተውም ቢሆን የራስ ቅልን የሙጥኝ ያሉ ሽበቶችም ከፍ ከፍ ይበሉ።

በ ትንሣዔ ተጻፈ

ሠኔ 2000